የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፩ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 30
ADDIS ABABA March 30th 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፭/፪ሺ፫
ብሔራዊ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት
ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.....ገፅ ፭ሺ፯፻፺፭

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፭/፪ሺ፫

## ብሔራዊ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፳፰ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል::

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "ብሔራዊ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፭/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር:-

፩/ በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፪ የተመለከተው ትርጓሜ ተፈጻሚ ይሆናል፤

፪/ "የመንገድ ትራፊክ ደህንነት" ማለት የመንገድ ተጠቃሚዎችና ማናቸውም ሀብት ከትራፊክ አደጋ የሚጠበቁበት ሁኔታ ነው፤

፫/ "ሚኒስቴር" ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ነው::

፫. **መቋቋም**

፩/ ብሔራዊ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚ ጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል::

፪/ ምክር ቤቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል::

፬. **ዓላማ**

የምክር ቤቱ ዓላማ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ስልቶችን በመቀየስ ለተግባራዊነቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላትን ማስተባበር ይሆናል::

፭. **የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር**

ምክር ቤቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ የተመለከተውን ዓላማ እውን ለማድረግ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

CONTENTS

Regulation No. 205/2011
National Road Traffic Safety Council Establishment
Council of Ministers Regulation ..........Page 5795

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 205/2011

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF NATIONAL ROAD TRAFFIC SAFETY COUNCIL

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 28 of the Transport Proclamation No. 468/2005.

1. ***Short Title***

This Regulation may is cited as the "National Road Traffic Safety Council Establishment Council of Ministers Regulation No. 205/ 2011".

2. ***Definitions***

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ the definitions provided under Article 2 of the Transport Proclamation No. 468/2005 shall be applicable;

2/ "road traffic safety" means the safeguarding of road users and any resource from road traffic accident;

3/ "Ministry" means the Ministry of Transport.

3. ***Establishment***

1/ National Road Traffic Safety Council (hereinafter the "Council") is hereby established.

2/ The Council shall be accountable to the Ministry.

4. ***Objective***

The objective of the Council shall be to devise road traffic safety strategy and coordinate the concerned organs for its implementation.

5. ***Powers and Duties of the Council***

The Council shall, in order to implement the objectives stated under Article 4 of this Regulation, have the powers and duties to:

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፩/ ብሔራዊ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፤

፪/ የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ለማሻሻል የሚመለከታቸው አካላትን ተሳትፎ ማጠናከር፤ የመንገድ ትራፊክ አደጋን ለመቀነስ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ተቀናጅቶና የበለጠ ውጤታማ ሆኖ እንዲከናወን ማስተባበርና ድጋፍ መስጠት፤

፫/ መንገድን፣ ተሽከርካሪንና የመንገድ ተጠቃሚን የሚመለከቱ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎች፣ ስታንዳርዶችና መመሪያዎች የመንገድ ትራፊክ አደጋን ከመግታት አኳያ ውጤታማነታቸውን በመገምገም የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ፤

፬/ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ትምህርት በመደበኛና በተጓዳኝ ትምህርት ውስጥ እንዲጠናከር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መተባበርና እንደአስፈላጊነቱ ድጋፍ መስጠት፤

፭/ የመንገድ ትራፊክ አደጋን ለመግታት የሚያስችሉ መድረኮች እንዲካሄዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ማካሄድ፤

፮/ የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ለማስፈን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ህብረተሰቡ የሚሳተፍበትን ሁኔታ ማመቻቸትና የብዙሃን መገናኛ ተሳትፎን ማጠናከርና እገዛ ማድረግ፤

፯/ በልዩ ልዩ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እንዲጠናከር ማድረግ፤

፰/ የሚመለከታቸው አካላት የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ለማረጋገጥ የነደፉትን ስትራቴጂና ፕሮግራም ውጤታማነት በየጊዜው በመከታተልና በመገምገም ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማቅረብ፤

፱/ የመንገድ ትራፊክ ደኅንነትን ለማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚመለከታቸው አካላት የተውጣጡ አባላትን የያዙ የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ማቋቋምና እንቅስቃሴዎቻቸውን ማስተባበር፤

፲/ ዓላማዎቹን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን::

፮. <u>የምክር ቤቱ አባላት</u>

የምክር ቤቱ አባላት ሰብሳቢውን ጨምሮ በመንግስት ይሰየማሉ::ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል::

፯. <u>የምክር ቤቱ ስብሰባዎች</u>

፩/ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በየስድስት ወሩ ይካሄዳል፤ ሆኖም በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል::

፪/ የምክር ቤቱ አብላጫው አባላት በስብሰባ ሲገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል::

1/ formulate national road traffic safety plans and programs;

2/ promote the participation of concerned organs to improve road traffic safety, and coordinate and assist them so that their joint efforts to reduce road traffic accident become effective;

3/ evaluate the effectiveness of existing laws, standards and directives regulating roads, vehicles and road users in deterring road traffic accidents and submit proposals to amend same;

4/ cooperate with the concerned organs and provide the necessary assistance to promote road traffic safety through formal and non-formal education;

5/ facilitate and organize forums on the prevention of road traffic accidents;

6/ in collaboration with the concerned organs, create conducive environment for the participation of the public, as well as encourage and assist the mass media to promote traffic safety;

7/ encourage private sector participation in different road traffic safety related activities;

8/ follow up and evaluate periodically the implementation of strategies and programs prepared by concerned organs to ensure road traffic safety, and submit reports to the Ministry;

9/ setup technical committees consisting of members from the concerned organs and coordinate their activities, as may be necessary to improve road traffic safety;

10/ carryout other related activities to attain its objectives.

6. ***<u>Members of the Council</u>***

Members of the Council, including the Chairperson, shall be appointed by the government; and their number shall be determined as necessary.

7. ***<u>Meetings of the Council</u>***

1/ Regular meetings of the Council shall be held every six months; provided, however, that extraordinary meeting may be held at any time when called by the Chairperson.

2/ The presence of the majority of members shall constitute a quorum for the deliberations of the Council.

፫/ የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል::

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

፰. <u>የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት</u>

፩/ ምክር ቤቱ በሚኒስቴሩ ውስጥ የተደራጀ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል:-

፪/ ጽሕፈት ቤቱ :-

ሀ) የምክር ቤቱ ሴክሬታርያት ሆኖ ያገለግላል፤

ለ) የምክር ቤቱን ጉዳዮችና ስብሰባዎች ሪኮርድ ይይዛል፤

ሐ) የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

መ) በመንገድ ትራፊክ ደህንነት ጥናት በማካሄድ የረጅም ጊዜ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማሻሻያ ኘሮግራም አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤

ሠ) የኘሮግራሙን አፈጻጸም በመከታተልና በመመዘን የማሻሻያ ሃሳብ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤

ረ) በሚመለከታቸው አካላት የሚቀርቡ የኘሮግራምና ስትራቴጂ አተገባበር ሪፖርቶችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፤

ሰ) የመንገድ ትራፊክ አደጋ መረጃዎችን ይተነትናል፤ የምክር ቤቱን ሥራዎች ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሕትመቶችን ያዘጋጃል፤

ሸ) በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ይፈጽማል::

፱. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ዕቅዶችን በመተግበር ረገድ ከምክር ቤቱ ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው::

፲. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ይህንን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሚኒስቴሩ ሊያወጣ ይችላል::

፲፩. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል::

አዲስ አበባ መጋቢት ፳፩ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3/ Decisions of the Council shall be endorsed by a majority votes; in case of a tie the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may adopt its own rules of procedure.

8. ***<u>Office of the Council</u>***

1/ the Council shall have an Office organized within the Ministry.

2/ The Office shall:

a) serve as the secretariat of the Council;

b) keep records of the affairs and meetings of the Council;

c) follow up the proper implementation of the decisions of the Council;

d) undertake studies in road traffic safety and prepare long-term action program for the improvement of road traffic safety and submit same to the Council;

e) submit proposals to the Council to update the action program through monitoring and evaluation of its implementation;

f) collect and compile the reporting of programs and strategies from the concerned organs;

g) analyze road traffic accident data and prepare publications necessary to achieve the objectives of the Council;

h) execute other duties as may be assigned to it by the Council.

9. ***<u>Duty to Cooperate</u>***

The concerned government organs and non-governmental organizations shall have the duty to cooperate with the Council in the implementation of traffic safety policy, strategy and programs.

10. ***<u>Power to Issue Directives</u>***

The Ministry may issue directives necessary for the proper implementation of this Regulation.

11. ***<u>Effective Date</u>***

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa this 30th day of March, 2011.

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*